# ከወይዘሮ ገነት ግርማ ጋር ቆይታ

ወ/ሮ ገነት ግርማን የማያውቁ ቢኖሩ ብዙዎች ይሆናሉ ተብሎ አይገመትም፡፡ ምክንያቱም ወ/ሮ ገነት ላለፉት ብዛት ያላቸው ዓመታት በሀገራችን ላይ ረቦ በቆየው የፖልቲካ ባህር ላይ ታግለው በማታገል መሃል ለምሃል የቀዘፉና የኢትዮጵያ ጉዳይ በሚስተናገዱባቸው ዓለም አቀፍ መድረኮች ላይም ብዙውን ጊዜ አለመለየታቸው ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች ናቸው፡፡ ወይዘሮ ገነት በትግሉም በትምህርቱም መስክ ችሎታቸውን ያስመሰከሩ ሲሆኑ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ፥ የኢሕአፓ መስራች አባል የአቶ ኢያሱ ዓለማየሁ ክብርት ባለቤት መሆናቸውና አስደናቂ በሆነ የታሪክ አጋጣሚም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጀርባ ላይና ከምድረ ኢትዮጵያ ጨርሰው ለማስወገድ አምረው የሚታገሉት የወያኔ/ኢህአዴግ መንግስት ፕሬዚዳንት የሆኑት መ/አለቃ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ አባታቸው መሆናቸው መጠቀስ ያለበት ነው፡፡



ለወ/ሮ ገነት ከሀገራችን ጉዳዮች ጋር የተያያዙ መሰረታዊ የሆኑ ጥያቄዎችን አንስተንላቸዋል፡፡ እሳቸውም የሚገባውን መልስ ሰጥተውናልና እነሆ መልካም ቆይታ ከማለታችን በፊት በዚህ ቃለ መጠይቅ ሂደት ላይ አንድ ከእሳቸው የታዘብነውን ነገር ሹክ እንበላችሁ፡፡ ከዚህ ቃለ-መጠይቅ ጋር የምናቀርበው አንድ በቅርብ ጊዜ የተነሳ ፎቶ ግራፍ እንዲልኩልን ተማጸንን፡፡ ፈቃዳቸው ሆነናም የፈለግነውን እንድንመርጥ የተለያዩ ፎቷቸውን ላኩልን፡፡ ለምርጫ የቀረቡልን ፎቶዎች ተመሳሳይ ባህርይ ይዘዋል፤ ጥቁር የሃዘን ልብስ ያጠለቁ ናቸው፡፡ ለጉብኝትና ለሥራ በየሄዱበት አገሮች የተነሷቸው ፎቶግራፎች ሳይቀሩ የሃዘን ልብስ ለብሰዋል፡፡ ለምን ብለን አልጠየቅንም፤ የተሰጠንን ተቀበልን እንጅ፡፡ ወይዘሮ

ገነት ጥቁር መልበስ ቢያዘወትሩም ባለፈው ታህሳስ ተናሽ ወንድማቸው ዲያቆን ሳምሶን ግርማ በአዲስ አበባ ማረፉንም ሰምተናል፡፡

እንግዲህ ወደሳቸው - ወደቃለ-መጠይቁ - እንመልሳችሁ፤ መልካም ቆይታ ብለናል....

__ሐዋርያ፡-__ ለረጅም ዓመታት በትግል ላይ በውጭ ሀገሮች መኖርዎት ይታወቃል፡፡ ከኢትዮጵያ ሁለገብ ታሪክ ወጣ ያሉ ነገር ግን ለሀገራችን ጠቃሚዎች ናቸው ብለው የተቀበሏቸው ማህበራዊ ግንኙነቶችና ኢኮኖሚያዊ ሥራቶች ካሉ ለሐዋርያ አንባቢዎች ቢያካፍሉን?

__ወ/ሮ ገነት፡-__ ባለንበት ዘመን በሌሎች ሀገሮች እያየ ለራሳችንም÷ ለሀገራችንና ለሕዝባችን የምንመኛቸው ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ በይበልጥ ደግሞ የሚያስቀናው ከእኛ ጋር ተመሳሳይ እድገትና ችግሮችም ያሏቸው ሀገሮች የሚሻሻሉበትን ጎዳና ሲጀምሩ ማየት ነው፡፡ ማህበራዊ ግንኙነትን አስመልክቶ የሕዝባቸውን ጤንነት ለመንከባከብና የትምህርትን ዕድል ለሁሉም ለማረጋገጥ የሚነደፉ ዕቅዶችን የመጀመርያ ስራቸው የሚያደርጉ መንግስታት በጣም የሚደነቁ ናቸው፡፡ ከድህነትና ከችግር መላቀቅ ጊዜ የሚወስድና ብዙ የዕድገት ደረጃዎችን የግድ የሚል ቢሆንም እስከዚያው ባለው እንኳን ጤንነትና ትምህርት የገቢ ምንጭ ላለውና ለሌለው በሚል ለግል መስክ የሚተዉ መሆን የለባቸውም፡፡ የኤኮኖሚ ስራቶችም የገበያውን መስክና የባለሀብቱን ጥቅም ብቻ የሚደግፉ ከሆኑ አደገኛ ነው፡፡ በተለይ እንደ እኛ ዓይነት ሀገሮች ጋ ሁለገብ ዕድገት የሚሰምርበትን ድልዳል የጣለ መንግስት ኖሮም ስለማያውቅና የሙስናም ባህል ሁሌም እንደተንሰራፋ በመሆኑ ባለጊዜዎች ስግብግብና ከአፍንጫቸው አርቀው የማያዩ አብዛኛው ተበድሎ፤ታርዞና ተርቦ አይተው እንዳላዩ ይሆናሉ፡፡ ሀገራችንን ከዚህ አሳፋሪና አሳዛኝ አዙሪት ማውጣት አለብን፡፡ በበኩሌ የሀገር ክብር በመጀመርያ የግለሰብ ዜጎች ክብርና መብት ጋር ካልተዛመደ ትርጉም ያጣል፡፡

__ሐዋርያ፡-__ ብዙውን ጊዜ በግልጽ ሲንቀሳቀሱ የሚታዩት በዓለም አቀፍ የሠብአዊና ዴሞክራሲያዊ መድረኮች ላይ ነው፡፡ ይህ ሃላፊነት በድርጅትዎ ተሰጥቶዎት ነው ወይስ እርስዎት የመረጡት ሌላው የአስተዋፅኦ ዘርፍ?

__ወ/ሮ ገነት፡-__ የሰብዓዊ መብት ጥያቄ በእኔ ግምት ከፍተኛና ልዩ ቦታ ሊኖረው ይገባል፡፡ እኛ በተመክሮ እንደምናየውና በህይወታችንም እንደምንኖረው ለውጥ ከመጣ--የግለሰብ ሆነ የመደራጀት ወዘተ መብት መከበር ጉዳይ እውን ከሆነ-- ለተወሰነ ክፍል ብቻ ሊሆን አይችልም፡፡ ወደኋላ የሚጎትቱንና ሀገራችን እንዳያልፍላት የሚያደርጉት ይሄንን የመሰለ የተሳሳተ አቅዋም የያዙ ለነሱ ሞልቶላቸውና አልፎላቸው ለሌላው ሲቀርበት ይታያቸዋል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ሁኔታ ማወቅ፤ለመገንዘብ መሞከርና ከዚያም ትምህርት መውሰድ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ በሳይንስና ቴክኖሎጂ እንደሚታየው በአንድ አካባቢ የተገኘ ዕውቀት የምንጋራው እንጂ እያንዳንዱ የራሱን ውጣ ውረድና ስህተት መድገም የለበትም፡፡ የማምንባቸውና ጠቃሚ በመሰሉኝ መስኮች ለመስማራት ኃላፊነት እስኪሰጠኝ አልጠብቅም፡፡የዓለም አመለካከትና የራስ ዓላማና አቅዋም ላይ ግንዛቤ ካለ እያንዳንዷ/ዱ ግለሰብ መስራት የሚችለውንና ያለባትን/ያለባቸውን ሃላፊነት አይስቱም ብዬ አምናለሁ፡፡ ከራስ አኗኗር ጋር አብሮ መራመድ ያለባቸው መርህዎች መሰረታዊና ማንነታችንንም የሚገልፁ ናቸውና፡፡

__ሐዋርያ፡-__ በሚሳተፉባቸው መድረኮች ሁሉ የሴቶች ተሳትፎ እንዲጨምር የሚያደርጓቸውን ጥሪዎች ተከታትለናል፡፡ ይህ ስለሴቶች ተሳትፎ ማሳሰቢያዎ አድማጭ አግኝቶ ፍሬ እያፈራ ይሆን? ለሴት እናቶቻችንና እህቶቻችን በቀጣይነትና በጽናት እንደርስዎት መሳተፍ አለመቻል ዋና ዋና ምክንያቶች ምን ይመስልዎታል?

ወ/ሮ ገነት፡- ሴቶች እናቶችና እህቶችና ልጆቻችንን ማየት ስለማንፈልግ ወይም አይናችንን ወደ እነርሱ በምናዞርበት ጊዜ ወደ ቁም ነገር ስለማናዘነብል እንጂ ይሳተፋሉ፤ይሰራሉ:: የጨለመበት ኋላቀር ዘመን እንደገና በመንሰራፋቱና የባህል ተፅዕኖ ከዚያው ጋር ስለሚሄድ ድርጅቶችና መድረኮች በሞላ የወንድ ልዩ ክበብ መስለዋል:: መሰረታዊ ከሆነው ቤተሰብን ከማስተዳደር ጀምሮ የግልን ኑሮ መግፋት፤ በሰፊው መስክ መሰማራት ሆነ በትምህርት መስክም ቢሆን ልብ ተብሎ ቢጠየቅ የሴቶች ታሳትፎ ከፍ ያለ ነው:: ዓለም በአጠቃላይና በየባህሉም በወንድ መነፅር የማየቱ ልምድ ስላለ የምንሰበስብቻው ሆኑ ስራዬ ብለን የምናተኩርባቸው ወንዶች ላይ ብቻ ሆነዋል:: ይሄንን ሁኔታ ለመቀየር ትንሽ ድልድይ ብቻ ነው የሚጎድለው:: ስለሆነም የሴቶች ቦታ ጓዳ ብቻ ተደርጎ መታየቱ ያመጣው ዓይነ ጥላ መገፈፍ አለበት:: ለነገሩ ካለፈው ግንቦት 97 ምርጫ ጀምሮ በሀገር ውስጥም ሆነ ባዕዳ ሀገሮች በታዩ የሕዝብ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች የሴቶች ሚና ከፍ ያለ መሆኑን በከፈሉት መስዋዕትነት ሳይቀር አሳይተዋል:: እንደ በፊቱ ከፖለቲካው መራቁ፤አንገትን መድፋቱ ቀርቷል:: ጊዜና ሁኔታን እንደቀድሞው ካደረግን ጠንካራና ጎበዝ ሴቶች በርከታ ናቸው:: ዋናው ችግር በህብረተሰቡ ያላቸው ቦታ ከወንዱ እኩል መሆኑን--ማለትም ግማሽ የህብረተሰቡ አካል መሆናቸውን- ማሳመኑ ላይ ነው::

ሐዋርያ፡- ባለቤትዎ አቶ ኢያሱ ዓለማየሁ ሌላው የትግል አባቶች ከሚባሉት አርበኞች መካከል አንዱ መሆናቸው ግልጽ ነው:: ለመሆኑ የሁለት ታጋዮች ጋብቻ ደስታውና ውጣ ውረዱ እንዴት ይሆን?

ወ/ሮ ገነት፡- ጋብቻ የሚለው ቃልና ትስስር በሚገባ መታየት ያለበት ነው::ከምናየው ታሳሪዋና ቀንበር ተሸካሚዋ፤መሰረታዊ ነገሮችና አርጊና ሰሪ ሴቷ በመሆኗ፤ህጎችና እምነቶችም ከወንድ ጥቅምና ፈላጎት አንፃር ስለተቃኙ ቅዋሜ መኖሩ የሚገባ ነው:: ልጆችን ከማሳደግ አንፃር እንኳን "እሱ ወንድ ነውና..." የሚለው ማዳላት በአለም አቀፍ ደረጃ አሁንም ቢሆን የሰፈነ ነው:: በበኩሌ የኑሮ ጓደኛን በተመለከተ እኩያ፤አብሮ ሀሳቢና ተላሚ፤ የልብና የስራ ጓደኛም የሚኮንበትን ጓደኝነት ነው እኔ የምደግፈው፤ የምቀበለው:: ከራስ አመለካካት፤አላማን ፍላጎት ጋር የሚጓዝ የኑሮ ጓደኛን ማፍራት የመሰለ ተዓምራዊ ነገር የለም:: በህይወታችን አንዳንዴ ወሳኝ ወሳኔዎችን በምንወስድበት ወቅት ነገሮች ተሳክተው ላይገኙ ይችላሉ:: ባስፈለገ ጊዜ መለያየትና አንዳንዴም በተለያየ አቅጣጫ እየነጎዱ በተግባር ላይ መዋሉ ብቸኝነትን ሊያሰማ ቢችልም ለመስራት የሚፈልገውን፤እምነቱንና ቁም ነገር የሚለውን ለይቶ ያወቀ ሰው ደላው አልደላው የተሟላ ህይወት ያለው ነው ብዬ አምናለሁኝ:: ማቴሪያላዊ ወይም የኑሮ ምቾት ባይጠላም የራስን ዓላማ ተመርኩዞ ለተሻለ ዓለም መከሰት ታታሪ መሆንን የሚተካ ነገር ያለ አይመስለኝም:: ለልጃችንም ያስተላለፈንላት ባህል ይኼው ነው ብዬ አምናለሁ::

ሐዋርያ፡- አንዳንድ ሰዎች እንደ እቴጌ ምንትዋብ (የአፄ ቴዎድሮስ ባለቤት) ሊቆጥሩዎት እንደሚያስቡ ታዝበናል:: ይኸውም አባትዎ በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ መንግሥት ፕሬዚዳንት የመሆናቸውን ሃቅና፥ እርስዎ ከባለቤትዎ ጋር ሆነው ይህን አባትዎ በበላይነት የተቀመጡበትን መንግሥት፥ የግፍ ሥርዓት ነው ብለው አምርረው በመቃወም ለማስወገድ የሚያደርጉትን የተፋፋመ ትግል በማገናዘብ ነው:: እባክዎትን የአባትና ልጅ ጣጣ በአገር ጉዳይና በፖለቲካ እምነት እንዴት ሊበጠስ እንደሚችል ለአንባቢዎቻችን ያስረዱልን?

ወ/ሮ ገነት፡- ከበፊቱ ጥያቄ ጋር ይያያዛል:: በበኩሌ እንኳን አሁን ዕድሜዬ ገፍቶ ይቅርና በወጣትነቴ ጊዜም ብሆን የሚመስለኝን ተናግሬ የምከራከር ሰው ነበርኩኝ:: ዘመዶቼም ይህን ይመሰክራሉ:: የአሁኑ አቀዋሜም በዘመናት ትግል ተመክሮ የዳበረና እምኜበትም በፅናት አንዴም ሳላቋርጥ የተጓዝኩበት ለመሆኑ ምስክር አያስፈልገኝም:: ስለዚህም ባልሆነ መንገድ የሄደ የመሰለኝን ሰው ያመልስማማበትን ከማስረዳትና ተከራክሮ ለማሳመን ከመሞከር ወደ ኋላ አልልም:: ይህን ስልም የስጋ ዝምድና ኖረ አልኖረ የሚለወጥ አይደለምም ለማለት

ነው። አዳዲስ ክስተቶች ተፈታታኝ ሆነው ለሚያስቸግራቸው ሰዎች ግር ይል ይሆናል እንጂ በበኩሌ በሀገሬ ላይ ደርሶ የምጠላውን ሆነ እንዳይሆን የምመኘውን በተመለከተ ብዥታ ኖሮኝም አያውቅም።

ሐዋርያ፡- በውጭ ሀገሮች ምን ያህል ኢትዮጵያዊ ሴቶች እንደሚገኙ የተካሄደ ጥናት ይኖር? በኑሮ ደረጃ ከወንድ ወገኖቻቸው ጋር እንዴት ይነጻጸራሉ?

ወ/ሮ ገነት፡- ኢትዮጵያውያን በዓለም ተዘርተዋል--በአውስትራሊያ ደቡብ አሜሪካ ሳይቀር። በዓለም ላይ በአጠቃላይና በተለይም በበለፀጉ አገሮች ሴቶች በትምህርት ደረጃ አንደኛነትን ከያዙ ከርመዋል።በተለይም በዩኒቨርሰቲዎች ከፍተኛ ውጤት በማምጣትና በታታሪነት እንደበለጡ ተጨባጭ ጥናቶችና አሀዞችም ያሳያሉ። በተጨማሪም ከዚህ ቀደም ለእነሱ ዝግ የነበሩ ወይም እንዲሄዱ ወደ ማይበረታቱበት የሳይንስ መስኮችም ገብተው ችሎታቸውን እያስመሰከሩ ነው። በግብረሰናይና የሰብዓዊ መብት አስጠባቂ ድርጅቶችም ቁጥራቸው መብለጥ ብቻ ሳይሆን ከሁለት ሶስተኛ በላይ መሆኑ በየዓለም አቀፍ ስብሰባው የሚታይና የሚነገርም ነው። በሀገራችን ሴቶች ገና መብታቸውን ማስከበር ስላልቻሉ ይህ ችሎታቸው በገሀድ ሊታይ ገና ዕድል አላገኘም። ጎጂ ባህሎችም የሴቶችን መብት ከማጓተት አንፃር አሁንም ከፍተኛ ሚና አላቸው። ስለዚህ ለውጥ ገና የሚጠበቅ ጉዳይ ሆኗል።

ሐዋርያ፡- ድርጅትዎን÷ ኢሕአፓን÷ የሴቶችን ጉዳይ በተመለከተ ከሌሎች ድርጅቶች ልዩ የሚያደርገው ነጥብ ይኖር?

ወ/ሮ ገነት፡- ኢሕአፓ ድርጅቴ ነው። በድርጅቱ ውስጥ በመኖሬና በመታገሌ/ ብቻ ብዙ ብዙ ትምህርት ቀስሚያለሁ። ሆኖም ግን የሕብረተሰቡ ውጤት በመሆኑና የመነጨበትም ሀገር ችግሮች የኢሕአፓም በመሆናቸው በሴቶች ጥያቄ ላይ ምንም እንኳን ድርጅቱ ከሌሎች ቢሻልምና አዎንታዊ አስተዋፅዖው የሚታወቅ ቢሆንም በበኩሌ ግን ዛሬ እኔ በምጠብቀው ደረጃ ላይ ገና አልደረሰም ለማለት እደፍራለሁ። ይሄ ገፅታው ደግሞ የሚጋነነው በዚህ ጉዳይ ላይ የቀድሞው ኢሕአፓ መሻሉ በግልፅ በተግባር በመታየቱ ነው። እንደ ኢህአፓ ለሴቶች መደራጀት የለፋ ድርጅት የለም አደርጅቶ አታግሎ በመላ አገር በመስራቱ በርካታ የበሰሉ የነቁና አገር ማስተዳደር የሚችሉ የሴቶች ትዉልድ ለአገራችን አፍርቷል። ሌላዉ ቀርቶ የወያኔ መንግስት እንኳን ስለሚቸግረዉ የሚያሰራዉ የድሮ አባሎቻችንን አይደለ እንዴ። ለልጆቻችን ማዉረስ የምንፈልገዉ አገርና አለም ከምናየዉና ከምናዉቀዉ የተቻለ እንዲሆን ማድረግ እንደምንችል አምነን ነዉ ለመታገል የምንችለዉ። ትገላችን ለትውልድ መሰረታዊ ለውጥ በመሆኑ-- በእኛ ዘመን ባናየውም እንኳን-- የድርሻችንን ማበርከት ተገቢና የሚጠበቅ በመሆኑ ጥረቱ መቀጠል አለበት።

ሐዋርያ፡- አሁን በሥልጣን ላይ ያለው የወኔ/ኢህአዴግ መንግሥት ኢትዮጵያን ወደ ዓለም አቀፉ መድረክ በማምጣትና በማቀራረብ ሚና ተጫውጫለሁ ይልላ። መቀራረብ ካለ በእኩልነትና በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ የተመሠረተ እንዳልሆነ ደግሞ ብዙዎች ይናገራሉ። እርስዎ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚጨምሩት ካለ ቢገልጹልን?

ወ/ሮ ገነት፡- ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ መቅረቧና መነሳቷ ብቻ በራሱ ትርጉም ያለው ነገር አይደለም። ባለፈ ታሪክና በነበረ ጀግንነት፤ሀገሪቷ ነፃነቷን ጠብቃ በመቆየቷ ብቻም በመኩራራት ዛሬ ካለንበት ችግር ልንወጣ አንችልም። አሸባሪ ስርዓት፤ ሺዎችን የሚያስርና የሚያሰቃይ መብት ረጋጪና አሳዳጅ ስርዓት ስር ነን። ሴቶች በተለይ በሁሉም መስክ መብታቸው ተረግጦ ለዘመናዊ ባርነትም እየተሸጡ ያሉበት ጊዜ ነው። ከዚህ መገላገል ያስፈልጋል። የሀገራችን ሉዓላዊነትን በሚጠብቅና ለህዝቧ ጥቅም በሚሆን መንገድና አቅጣጫ የውጭ ጉዳዩ ስራ ሲካሄድ እስካሁን አልታየም። በዚህ ሁኔታ ከውጭው ዓለም

መቀራረብ የሚለው አገራችንን ለባዕዳን ጥቅም በርግዶ በመስጠት የተወሰኑ ግለሰቦችን በሌብነት ማክበር ነው ውጤቱ:: የሚያሳዝነው ደግሞ ኢትዮጵያ አሉ የተባሉትን ዓለም አቀፋዊ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች የፈረመች ሆና የትኛውም ግን በምድሯ የማይከበርባት መሆኗ ነው:: በተለይም ዜጎቿ በገዛ ሀገራቸው ከባዕዳን ያነሰ መብት ያላቸው መሆኑ የሚያሳዝ ነው::

ሐዋርያ፡- በተለያዩ ድርጅቶች መካከል (ኢሕአፓን ጨምሮ) እስካሁን ሕዝብና ሀገሪቱ የሚመኙት ጠንካራ ሁሉን አቀፍ ህብረት አልተመሠረተም:: ይህን በተመለከተ የሚሰጡት ምክር ምንድን ነው?

ወ/ሮ ገነት፡- ባለፉት 30 ዓመታት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጀቶች ብዙ ተመክሮ አካብተዋል:: ይህ ከታሪክና ከሌሎችም ሀገሮች ተመክሮዎች ሲነፃፀር አጭር ጊዜ ነው:: ከእነ ጭራሹ የፖለቲካ ድርጅት ሊመሰረት ሊሞከር ቀርቶ ተቃዋሚ ነኝ ማለት ራሱ አስፈሪና ጎጂ የነበረበትን ዘመን ብዙዎቻችን እናስታውሳለን:: አፈናው ቢቀጥልም ዛሬ የተለየ ሁኔታ አለ :: ከዚህ አንፃር ሲታይ ለህብረት ብዙ ጥረቶችና ሙከራዎች መደረጋቸው ጥሩ ጅምር ነው ማለት ይቻላል:: በቁም ነገር የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ ከሚኖሩ ሰዎች ብዙ ሊጠበቅ ይገባ እንደሆነ እንጂ በየክረምቱ እንደሳር ብቅ የሚሉትን ሁሉ በቁም ነገር መተቸት አይቻልም::ደምበኛ ግንዛቤን ለማግኘትና የቁም ነገር ደረጃውን የጠበቀ ውይይት ለማካሄድ ብስለትን ይጠይቃል:: ያም ሆነ ይህ ግን እጅን አጣጥፎ መቆዘም የሚያስገኘው ውጤት ስለሌለ አሁንም ሁሉን አቀ ፍ ጠንካራ የተቃዋሚ ህብረት እንዲገነባ መጣር ከሁላችንም ይጠበቃል::

ሐዋርያ፡- ሊያስተላልፉት የሚፈልጉት የተረሳ መልእክት ካለ?

ወ/ሮ ገነት፡- የማስተላልፈው መልዕክት ቢኖር ተባብረን ይህንን አስከፊ ሁኔታ በትግል በመቀየር ሀገራችንን እንጠብቅ፤ዴሞክራሲን እናስፍን የሚል ነው:: ሴቶች በተለይ ለመብታችን ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ተደራጅተን መታገል አለብንና ዕድል አግኝተው የነቁት ሴቶች እህት እናቶቻቸውን በማንቃትና በማደራጀት የጋራ መብታችንን እንደናሰምር የትግል ጥሪ አሰማለሁ::